# ጥላ

ዋና ስራ አስኪያጅ — General Manager

መስፍን አብርሃ — Mesfin Abraha

## ዋና አዘጋጆች — Editor In Chiefs

እየሩሳሌም ሱሞሮ — Eyerusalem Sumoro
ዳዊት ፋንታ — Dawit Fanta
ደሳለኝ አበበው — Desalegne Abebew

## አዘጋጆች — Editors

ደበበ ከበደ — Debebe Kebede
ፍስሃፅዮን ሃይለገብርኤል — Fisshatsion Hailegeberile
ህሊና ዳዊት — Hilina Dawit

## ጽሁፍ አስተባባሪዎች — Coordinators

ብርሃኑ ባዩ — Berhanu Baue
በተወዳጅ አድነው — Betewedag Adnew
ዮሐንስ ሰላሙ — Yohannes Selamu

የኮምፒዩተር ፅሁፍ ቅንብር — በዝግጅት ክፍሉ

የጥላ መጽሔት አድራሻ/
Tila Magazine Address
Mesfin Abraha
An der Obergeis 1
36251 Bad Hersfeld
Email:- tilamagazine@yahoo.de
Web-Site:- tilamagazine.yolasite.com
Tel.No.:- 015222195567, 015214528602, 015219261884

# ማውጫ


ከቢን ላደን ግድያ በስተጀርባ 6

ኢትዮጵያ በጋዜጠኞች... 10

በስደትም አንደኛ? 10

የወያኔ ፍትሃዊ ምርጫ! 10

መሬት ቆርሶ ... 10

የአገር ስሜት ሳይኖረው 11

አምባገነኑ ወያኔ 11

በደሉ ስር ሰዷል 11

ጅምላ መፈናቀል... 11

ኢትዮጵያ ትቅደም 12

ፑሽኪን ኢትዮጵያዊ ነው 12

ያሁኑ ይባስ 12

ካርቱን 13

Fair election….. 14

Private Press... 14

Innocents are still... 14

A closed window of opportunity for the coming election in Ethiopia 15

The Ethiopian authorities using repressive ... 15

Solidarity for freedom and justice in Ethiopia… 16

Attack on critical voices 16


**መልካም ንባብ**
**ጥላ መጽሔት**

## Where the press is free and every man able to read, all is safe.

**Thomas Jefferson**

# ABOUT TILA

**R**ealizing the fact that the digital age has empowered and made ordinary people across the world irrepressible beyond their imagination, **WE** aims to serve as a credible platform that will spread uncensored interviews, news, commentaries and analyses that are unlikely to see daylight in Ethiopia.

Fortunately, here is where you find **TILA**, the un-disputably best source of information serving the Ethiopian Diaspora community in Europe & America with a proven record of excellence in journalism.

**TILA** is a political magazine published and distributed by patriotic Ethiopians around Hessen region in Germany. **Tila** appears in Amharic, English and Germany Languages every 3 months. It is a magazine of quality, responsibility and standard. Entertainment and sport are among our coverage issues next to Ethiopian politics.

As a reader, you are to get useful political and current news in **TILA** than any other publication can offer you. More comprehensive analysis and interpretations than any other media can present to you. In fact, these are some of the qualities of **TILA** that has made it the largest circulating magazine in its category. **TILA** magazine has also partnered with ethiomedia.com, ethiogermany.de, ethiopiazare.com and afroaddis.wordpress.com, goolgule.com among others, to deliver reliable and high quality content to our visitors. The articles which are posting here doesn`t represent the Magazine`s Editorial committee, rather the writers.

Don't take the chance of missing this spectacular political magazine. Subscribe to it today! We promise, you won't regret your decision. Reach us on tilamagazine@yahoo.de & tilamagazine.yolasite.com

## Tila Magazine is yours Magazine!


## ውድ አንባብያን

ጥላ መጽሔት በየሶስት ወሩ የሚታተም የፖለቲካ መጹሔት ነው።መጽሔቱ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ መሰረት አድርጎ በጀርመን አገር የሚታተም ቢሆንም መረጃ መረቦችን በመጠቀም መላውን ዓለም የማዳረስ ዓላማን አንግቦ እየተንቀሳቀሰ ነው።

የአገራችንን ወቅታዊ ሁኔታና ጠቃሚ መረጃዎችን በማካተት ዝናን ያተረፈው የጥምረት መጽሔት አዘጋጆች ያቋቋሙት ጥላ መጽሔት የስሙ ስያሜ እንደሚያመለክተው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች በተበታተነ ሁኔታ የሚያካሂዱትን የትግል ሂደት በማስቀረት በአንድ ጥላ ስር እንዲሰባሰቡ ለማሳሰብና አቅጣጫ ለመጠቆም ነው።

የፖለቲካ ሃይሎች በተበታተነ ትግላቸው ጋት እንኳን መራመድ እንደማይችሉ በመገንዘብ የጋራ ትግል እንዲያካሂዱ ለማበረታታትም ጭምር ነው እ.ኤ.አ ከጥር 2012 ጀምሮ በዚህ ስም መጽሔቱ እንዲጠራ የወሰንነው።በመጽሔቱ አዝናኝና አስተማሪ ዝግጅቶች የሚካተቱበት ሲሆን ስፖርትም ትኩረት ያገኛል። ጥላ መጽሔት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሃሳቡን ያለምንም ገደብ በነፃነት የሚያቀርብበት ክፍት መድረክ በመሆኑ በመጽሔቱ የሚወጡት ፅሁፎች በሙሉ የፀሃፊዎቹን እንጂ የጥላ መጽሔት ዝግጅት ክፍልን የማይመለከቱ መሆናቸውንም መግለፅ እንወዳለን።

## ጥላ መጽሔት የእናንተው መጽሔት ናት!



# ርዕሰ አንቀጽ



# ከምርጫው የዜጎች ክብር ይበልጣል

ባለፉት ስድስት ወራት ብቻ የኢትዮጵያ መንግስት በርካታ ጋዜጠኞችን የፖለቲካ ሰዎችንና ጦማሪዎችን አስሯል።ሌሎችንም በአደባባይ በማስፈራራት ጭምር ጽህፈት ቤቶቻቸው ጭምር እንዲዘጉ አድርጓል።በጠንካራ ትችቱ የሚታወቀው አዲስ ጉዳይ መጽሔትም ከህትመት ታግዷል።በርካታ ጋዜጠኞችም አገር ጥለው የፖለቲካ ጥገኝነት ፍለጋ ወደ ተለያዩ አገራት ተሰደዋል።

በኢትዮጵያ መንግስት በቁጥጥር ስር የዋሉት የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎና ፖለቲከኞች አዲስ አበባ ውስጥ በተደጋጋሚ ፍርድ ቤት ቢቀርቡም ከተወሰኑት በስተቀር ህግ ከሚያዘው በላይ ፖሊስ የጊዜ ቀጠሮ እየጠየቀባቸው በእንግልት ላይ ይገኛሉ።ክሱ ግልፅ ባይሆንም እንዳለን መረጃ ከሆነ ግለሰቦቹ በውጭ ከሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች ጋር በመመሳጠር በማህበራዊ ድረ-ገጾች ሁከት በማስነሳት በአገሪቱ አለመረጋጋት ሊፈጥሩ ሲሉ ተደርሶባቸዋል የሚል ነው።ይህ ደግሞ ከእውነት የራቀ የፈጠራ ክስ ከመሆን አይዘልም።ለዚህም ነው እስካሁን ፖሊስ ማስረጃ ማሰባሰብ ያቃተው።


እኛም በተደጋጋሚ በፕሬስ ነፃነትና ሃሳብን በነፃ የመግለጽ መብት ላይ መንግስት እያከበደው የመጣውን ሰዶ ማሳደድ በመመልከት ቅሬታችንን ስንገልጽ ቆይተናል።ቢሆንም እንግልቱ እስሩና ማስፈራራቱ እንደቀጠለ ነው።ጋዜጠኞቹ ጦማሪዎቹና ፖለቲከኞቹ ከእስር በሁዋላ ከግል ጠበቆቻቸውና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ተገናኝተው ምክር ማግኘት አልቻሉም።መብቱ ግን በአገሪቱ ህገ መንግስትና በሌሎችም አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች ላይ በግልፅ ሰፍሮ ይገኛል።

በዚህ አመት ይካሄዳል ተብሎ በሚጠበቀው አገራዊ ምርጫ ምክንያት ኢህአዴግ የፕሬስ ነፃነትን ለማፈን የሙያውን ባለቤቶች ሞራል በመደፍጠጥ ስራ ላይ ከወዲሁ ተጠምዷል።አብዛኞቹ የመገናኛ ብዙሃን አባላትም በጸረ-ሽብር ህጉ መሰረት ከ5-እድሜ ልክ እስር ተፈርዶባቸዋል ወይም በዚሁ የሚያስቀጣ አንቀጽ ተጠቅሶባቸው ተከሰዋል። የኢትዮጵያ ባለስልጣናት እነዚህን በሞራልም ይሁን በሕግ ተቀባይነት የሌላቸውን “ሕጎች” በመጠቀም ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ የመደራጀትና የመሰብሰብ ነፃነቶችን እየገደቡ ናቸው።

የዓለም አቀፉን ተቋማት የፕሬስ ሁኔታ መረጃ ቢመረምሩ በአገራችን ከማፈር ሌላ አማራጭ የሎትም።በጣም ጭራ ከሚባሉት አገራት ተርታ ተመድባ ትገኛለች።በአንፃሩ ጋዜጠኞችን በማሰርና ጋዜጦችን በማገድ ከዓለም ግንባር ቀደም የወቅቱ ባለሪከርድነቱን ከኤርትራ ተረክባ ትገኛለች።

አሁንም የኢትዮጵያ መንግስት ጋዜጠኞችን ጦማሪዎችንና የፖለቲካ እስረኞችን መብታቸውን ስለተጠቀሙ ብቻ የበየነባቸውን እስር በማንሳት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲለቃቸው ጥሪያችንን እናቀርባለን። ፈቃድ የከለከላቸውን ጋዜጦችና ቢሮአቸውን የዘጋባቸውን ተቺ የፕሬስ ውጤቶችንም በር እንዲከፍት እንጠይቃለን። መጪው ምርጫ ሰዎችን ለእስርና ለስደት የሚዳርግ ከሆነ ይቅርብን።ከምርጫው የስራ አጋሮቻችንና ህዝቡ ይበልጣሉና።ፕሬሱን ከስቅላት ያድኑ! እንደ ሁሌው ጥላ መጽሄታችሁ በርካታ ዓለም አቀፍና አገራዊ ጉዳዮችን አካታ ለህትመት በቅታለች። መልካም ንባብም ትመኛለች።

**ጥላ መጽሔት የእናንተው መጽሔት ናት!**



# EDITORIAL



## Election costs Ethiopian journalists…..

The last 6 months only, the government has charged a lot of Journalists and political figures and also denied a permission or closed some of very critical newspapers including Addis Guday Magazine. Most of the journalists are also flee to different countries to get a political asylum.

The media people who were caught handed by the government of Ethiopia appeared before the Court in Addis Ababa. Although the exact charges against each of them remain unclear, we have received information that they were arrested for "working with foreign human rights organizations and inciting violence through social media to create instability in the country." This is a day light fabricated accusation.

**We** expressed often concerns about the increasing restrictions placed on freedom of opinion and expression in Ethiopia, following the recent arrest and detention of journalists bloggers and civil society activists`. After the imprisonment of the media peoples, they have no right to communicate their own lawyers and families to get some advices. This right is clearly indicated on the Ethiopian constitution and other international human right conventions too.

Because of the so called election 2015, EPRDF has already started to demoralized the media professionals to dismissed the right of freedom of expression. Most of the media people have been convicted under the Anti-terrorism Proclamation to sentences ranging from 5 years to life imprisonment.

The Ethiopian authorities use these morally and legally unacceptable ``LAWS`` to restrict the rights to freedom of expression, association and assembly.

If you are checking the press freedom index of international organizations, you will be ashamed of our country .it is very bottom. And number one by denying a permission and charging journalists in the world.

We urged the Ethiopian Government to release all bloggers and journalists currently in detention for simply exercising their right to freedom of expression. And the gov`t should have to give the work permission and to open the closed offices of very critical Newspapers and magazines. We don`t need the coming election. Our professional colleagues are worth than it !**Rescue press freedom from hanging!**As always Tila wish you a nice reading.

**TILA MAGAZINE IS YOURS MAGAZINE !**

# ከቢንላደን ግድያ በስተጀርባ(ክፍል ሁለት)

**Dawit Fanta (Engineer)/Germany**

***በባለፈው እትማችን የኦሳማ ቢንላደን አባት መሃመድ ቢን አዋድ በየመን በ1930 ዓ.ም. በተከሰተው ድርቅ ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ እንደተሰደደ ገልፀን ነበር ያቆምነው።ቀጣዩ ክፍል ከዚህ በታች ይቀርባል መልካም ንባብ።***

መሀመድ ቢን አዋድ በኢትዮጵያ የአጭር ጊዜ ቆይታ ካደረገ በኋላ በቀይ ባህር በኩል በማድረግ በጀልባ በምዕራባዊ የሳኡድ አረቢያ ዳርቻ ወደምትገኘው ጂዛን የገባ ሲሆን በግመል ሰረገላ ከሚጓዙ የሳዑዲ ነጋዴዎች ጋርም ወደ ጅዳ ተጓዘ።

በወቅቱ ሳዑድ አረቢያ በተለያዩ የጎሳ መሪዎች የምትመራና አንድነቷም ያልተጠናከረ ከመሆኑ ባሻገር በአለም ከሚገኙ ፍፁም ደሃ አገሮች አንዷ ነበረች።ይህችን በረሃ እና ድህነት እጅ ተወርች ጠፍንገው የያዟትን ሀገር በበላይነት ያስተዳድር የነበረው አብዱልአዚዝ ቢን አብዱልረህማን ቢን ፈይሰል አል ሳዑድ ሲሆን የሃገሪቱ ኢኮኖሚ የተመሰረተውም ከተምር የወጪ ንግድ /Export/ እና ለአመታዊ የሃጅ ጉዞ ከሚመጡ ሙስሊሞች ከሚገኝ ገቢ ላይ ነበር።ከድህነት እና በረሃማነት በተጨማሪ ሀገሪቱን የሚፈታተነው ስር የሰደደ የውሃ ችግር ሲሆን ንጉስ አብዱልአዚዝም ይህን ችግር ለማስወገድ በአሜሪካዊው ጂኦሎጂስት ካርል ትዊቼል በተመራ ቡድን በሳዑድ አረቢያ ከርሠ ምድር ውስጥ ውሃ አልያም ወርቅ እንዳለ ጥናት ያስደርጋሉ።ነገር ግን የጥናቱ ውጤት የሀገሪቱ ከርሠ ምድር ውሃም ሆነ ወርቅ የሌለው መሆኑን ሲያሳይ በተቃራኒው ከፍተኛ የሆነ የነዳጅ ክምችት እንዳለው ይረጋገጣል።

ይህም ዛሬ ለምናያት የሀብታሞች ቁንጮ ለሆነችው ዘመናዊት የሳዑድ አረቢያ ኪንግደም ኢኮኖሚ የማዕዘን ራስ ሆነ።በዚህም መሠረት "አራምኮ" በመባል የሚታወቀው የነዳጅ እና የግንባታ ድርጅት በሁለቱ ሀገራት ትብብር ሲቋቋም በጅዳ የወደብ ሠራተኛ ሆኖ ይሰራ የነበረው መሀመድ በዚሁ ድርጅት በግንበኝነት ተቀጠረ።በሂደትም በ1950ዎቹ የተስፋፋው ከፍተኛ የነዳጅ ቁፋሮ ዕድገት የቀድሞውን በረሃማ የአረቢያ ልሣነ ምድርን ወደ ምድራዊ ገነትነት ሲያሸጋግረው የሳዑዲ መንግስትም በአሜሪካኖቹ ላይ ባደረገው ጫና አራምኮ ለአረብ ተወላጆች የሙያ ስልጠና እንዲሰጥ ከማስደረጉም ባሻገር በስሩ የሚገኙትን ጥቃቅን ፕሮጀክቶችን በንዑስ ኮንትራት በመስጠት አረቦቹም ከተቀጣሪነት በዘለለ የኢኮኖሚ ዕድገቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደረገ።ከነዚህ መካከል መሀመድ ቢን አዋድ አንዱ ሲሆን በተለይም በጅዳ የሚሰራቸው ቤቶች የወቅቱ የፋይናንስ ሚንስትር የነበሩትን ሼህ አብዱላህ ቢን ሱለይማንን ትኩረት መሳብ ጀመረ። በመሆኑም በእኚሁ የፋይናንስ ሚንስትር አማካኝነት የመሃመድ ቢን አዋድ የሥነ ህንፃ ጥበብ ከንጉስ አብዱልአዚዝ ዘንድ የደረሰ ሲሆን ንጉሱም በጅዳ የሚገኘውን ቤተመንግስታቸውን እንዲያድስ ኮንትራት ሰጡት።መሃመድም የንጉሱን በዕድሜ መግፋት ከግምት በማስገባት እስከመኝታ ክፍላቸው ድረስ



መኪናቸውን ማስገባት የሚችል መረባርብ /Ramp/ በመስራት ንጉሱን ሲያስደምም ይኸው አጋጣሚም በሳዑዲ ንጉሳውያን ቤተሰብና በቢንላደን ቤተሰብ መካከል እስከዛሬ የዘለቀ የንግድና ጥቅማጥቅም ግንኙነት እንዲመሰረት ፈር ቀዳጅ ሆነ።

ንጉስ አብዱልአዚዝ ሞተው በንጉስ ሳዑድ ቢተኩም የመሀመድ ቢን አዋድና የንጉሳውያን ቤተሰቡ የጥቅም ግንኙነት ይበልጥ እያደገ ከመምጣቱም በላይ የመሀመድ ኢንቨስትመንት የሳዑዲን ድንበር ተሻግሮ መካከለኛው ምስራቅን ማዳረስ ጀመረ።መሀመድም በተለያዩ ሀገራት ለስራ መመላለስ የዕለት ተዕለት ተግባሩ ሲሆን ሶሪያም አንዷ መዳረሻው ነበረች።እናም በ1956 ዓ.ም. ከሀገረ ሶሪያ አራተኛ ሚስት ትሆነው ዘንድ የአስራ አራት /14/ ዓመቷን አሊያ ጋኔምን አግብቶ ወደ ሪያድ አመጣት።ከሁለት አመት በኋላም በወርኃ ጥር ለመሃመድ አስራሰባተኛ /17ኛ/ ለአሊያ የመጀመሪያ የሆነው ወንድ ልጅ በሪያድ ተወለደ፤ ለስም አጠራሩም **ኦሳማ ቢን መሐመድ ቢን አዋድ ቢን ላደን** ሲሉ ሰየሙት።ትርጓሜውም "አንበሳ" ማለት ነው (ኦሳማ፦ አንበሳ፣ብርቱ ተዋጊ፣ጠንካራ........ እንዲል የአረብኛው ግስ)።

ይሁን እንጂ ኦሳማ የ5 ዓመት ልጅ እያለ የወላጆቹ ትዳር የፈረሰ ሲሆን አሊያ ጋኔምም ከነብዩ መሐመድ (ሰለላሁ አላሂ ወሰላም) የዘር ሀረግ የሚመዘዝ መሃመድ አል አታስ የሚባልን ሰው ስታገባ ባለ ብዙ ሚስት፥ባለ እልፍ ውሽማ የሆነው የኦሳማ አባት መሐመድ ቢን አዋድም ሃያ ሰባተኛ /27ኛ/ ሚስቱን ለማምጣት በአውሮፕላን እየተጓዘ ሳለ አውሮፕላኑ በመከስከሱ የህይወቱ ፍፃሜ ሆነ። ኦሳማን ጨምሮ ሌሎች የመሀመድ ቢን አዋድ ልጆች የዚህ አይነቱን ሰፊ የንግድ ኢምፓየር በራሳቸው ለማስተዳደር የዕድሜም ሆነ የዕውቀት ውስንነት በመኖሩ ንጉሱ የባለአደራ ቦርድ በማቋቋም ለቀጣይ አስር አመታት ቤተሰቡና የንግድ ተቋማቱ በዚህ የአደራ ቦርድ ጥበቃ ሥር እንዲተዳደር አደረጉ።በመሆኑም ከኦሳማ በቀር ሌሎች የመሀመድ ቢን አዋድ ልጆች ወደ ተለያዩ ሀገራት ተልከው ትምህርት የተማሩ ሲሆን ኦሳማም በጅዳ አልታግር ጎዳና በሚገኝ ስመ ጥር

ትምህርት ቤት ትምህርቱን መከታተል ጀመረ።

ነገር ግን የአስራ አራት /14/ ዓመት ልጅ እያለ በሶሪያዊው የጂም መምህሩ አማካኝነት እስላማዊ አብርሆትና ፖለቲካዊ መነቃቃትን ማዳበር ጀመረ። በዚያው ወቅት አካባቢም በሳዑድ አረቢያ በህቡዕ ይንቀሳቀስ የነበረውን የሙስሊም ወንድማማቾች ህብረትን ተቀላቀለ። በተለይ በዚያን ወቅት የሙስሊም ወንድማማቾች ፍልስፍና በሁለት ጎራ ተከፍሎ ከፍተኛ ክርክር ይደረግ የነበረ ሲሆን በአንድ በኩል የቀኝ ክንፍ የአክራሪነት ዝንባሌ ያለውንና በሰኢድ ቁትብ የተቃኘውን አመለካከት ሲደግፉ በሌላ በኩል ግራ ዘመም የሆነውንና መቻቻልን የሚሰብከውን እንዲሁም የሰኢድ ቁትብን አመለካከት በመተቸት የሚታወቀውን በሀሰን አል ሁዳይቢ የሚዘወረውን ሥነ ሀሳብ የሚደግፉ ነበሩ። ኦሳማም የሰኢድ ቁትብን ፍልስፍና የሚከተል ሲሆን በኋላም እንደ አማራጭ ለወሰደው የፅንፈኝነት መንገድ ይኸው አመለካከት ተፅዕኖ ሳያሳድርበት እንዳልቀረ ይገመታል።

በ1976 ዓ.ም. ጅዳ በሚገኘው የንጉስ አብዱልአዚዝ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ የኢኮኖሚክስ ትምህርቱን የተከታተለ ሲሆን በዩኒቨርሲቲ ቆይታው በተለያዩ ሃይማኖታዊ በጎ ተግባራት ከመሳተፉ ባሻገር በቁርአን ትርጓሜና በጅሃድ ትንታኔ ላይ ሰፊ ጊዜውን ሰጥቶ ይከታተል እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በገና ዋዜማ 1979 ዓ.ም. የዓለምን ህዝብ ጆሮ ጭው የሚያደርግ ዜና ከወደ ማዕከላዊው ኤዥያ ተሰማ። ይኸውም "ቀዩ ጦር" በመባል የሚታወቀው የቀድሞዋ ሶቭየት ህብረት ጦር ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎቹን በማስከተል በሜካናይዝድ ደረጃ የአፍጋኒስታንን ድንበር ሰብሮ ግልፅ ወረራ ፈፀመ። ይህ የሶቭየት ወረራ ለተለያዩ ቡድኖች የተለያየ ትርጉም የነበረው ሲሆን በእስላማውያኑ ዘንድ እስላማዊት አፍጋኒስታን "በአምላክ የለሽ" ኮሚኒስቶች ተወረረች ብለው አፊሻል ያልሆነ ጅሃድ ሲያውጁ በቬየትናም ጦርነት በሶቭየት ላይ ቂም ቋጥራ ለነበረችው አሜሪካ ጂሃዲስቶችን በድብቅ በመርዳት ሶቭየትን የምታዳክምበት የገና ስጦታ ነበር። በመሆኑም ከደቡብ ኤዥያ፣ከሰሜን አፍሪካ እና ከመካከለኛው ምስራቅ




የሚገኙ ጂሃዲስቶች በዚህ "ቅዱስ" ጦርነት ለመሳተፍ ወደ አፍጋኒስታን መትመም ሲጀምሩ የሳዑዲ መንግስት የአውሮፕላን ቲኬት ወጪን ከመሸፈን ጀምሮ የ10 ዓመቱ ጦርነት እስካበቃበት ጊዜ ድረስ ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍ ያደርግ የነበር ሲሆን ኦሳማም የሳዑዲ መንግስትን ኦፊሻል ባልሆነ መንገድ በመወከል ይህንን እርዳታ በየጊዜው ከማድረሱ ባሻገር በጅዳ የሚገኘው የመኖሪያ ቤቱን ጂሃዲስቶችን ለመመልመልና ወደ አፍጋኒስታን ለመላክ የቀድሞ የዩኒቨርሲቲ መምህሩ አብዱላህ አዛም እንዲጠቀምበት እስከመፍቀድ ደርሶ ነበር።

የሳዑዲ የገንዘብ ድጋፍና የአሜሪካውያኑ ስቲንገር ሚሳኤሎች ብቻቸውን የሶቭየትን ጦር ማሸነፍ እንደማይችሉ የተረዱት አሜሪካውያኑ ከሳዑዲ መንግስት ጋር በመሆን አንድ የሴራ ድር መሸረብ ጀመሩ። ይኸውም ለተወሰኑ አመታት የነዳጅ ዋጋን እንዲያሽቆለቁል በማድረግ ከግማሽ በላይ የሚሆነው ዓመታዊ ገቢዋ በነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሽያጭ ላይ የተመሰረተውን የሶቭየትን ኢኮኖሚ በማዳከም ላይ ያነጣጠረ ሲሆን በተለይ ከነፃ ገበያ ይልቅ በዕዝ ኢኮኖሚ ለሚመራው የሶቭየት አስተዳደር ይህ የኢኮኖሚ ጦርነት የመጨረሻው መጀመሪያ መድረሱን አመላካች ነበር። በሌላ በኩል ሳዑድ አረቢያም በዚህ ቀድሞ በተሰላ ኪሳራ /Calculated Risk/ ወላፈን በከፊል የመለብለብ አደጋ ሲገጥማት በተለይ የወጣት ስራ አጥ ቁጥር ማሻቀብ ማህበራዊ ድብታን /Social Distress/ ፈጠረ። ይህንን ማህበራዊ ድብታ እንደ አንድ አጋጣሚ በመጠቀም ኦሳማ ቢን ላደን በመስጊዶች አካባቢ በመገኘት በተስፋ ማጣት ለሚዋልሉ ወጣቶች ቀስቃሽ ንግግሮችን ያደርግ የነበር ሲሆን በተለይ የሙስሊም ወንድማማቾች የፍልስፍና አባት የሆነው ሰኢድ ቁጥብ "ማይልስቶን" በሚል መጽሐፉ ያሰፈረውን ሃሳብ በማስተጋባት "***የአረቡ አለም ውድቀት ትልቁ መንስኤ እስልምናን የኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊ፣ማህበራዊና መንፈሳዊ ህይወታችን ገዢ ሃይል እንዳሆን አለማድረጋችን ነው፤ ይህንን ጥረትም ተግባራዊ እንዳናደርግ የምዕራቡ ዓለም ሀገራት በተለይ አሜሪካ ትልቅ ጋሬጣ ሆናለች***" እያለ ይቀሰቅስ ነበር። በዚህም አብዛኛው የሳዑዲ ወጣቶች ይህን ወጣት ሼህ ቋጠሯቸውን የሚፈታ፥ታሪካቸውን የሚገለብጥ "መሲህ" አድርገው ሲመለከቱት ለሳዑዲ መንግስትና የደህንነት ሰዎች ኦሳማ ጣቱን ወደ ውጪ "ጠላት" እስከቀሰረላቸው ድረስ አደጋ ያዘለ ትኩረትን የሚሻ አጀንዳቸው አልነበረም።የሶቭየት ጦር አስር አመት የፈጀውን የአፍጋኒስታን ጦርነት በታላቅ ኪሳራ ባጠናቀቀ ማግስት ኦሳማ ቀጣይ ዕቅድ አለኝ ሲል የሳዑዲ የደህንነት ሚንስትር ወደሆኑት ልዑል አልጋወራሽ ተርኪ ዘንድ ቀረበ። ይኸውም በወቅቱ የመን ልክ እንደ ኮሪያ ሁሉ ሁለት ሀገር ሆና ሰሜንና ደቡብ የመን ተብላ የምትጠራ ስትሆን ደቡብ የመን በአረቡ ዓለም የምትገኝ ብቸኛዋ ኮሚኒስት ሀገር ነበረች። የኦሳማም ዕቅድ ከአፍጋን ዘመቻ የተመለሱትን ሙጃህዲኖች በማስተባበር የአባቱ ሀገር የሆነችውን ደቡብ የመን ከኮሚኒስቶች መዳፍ በማውጣት እስላማዊ መንግስት እንዲመሰረት ማድረግ ሲሆን የደህንነቱ ሰው ሃሳቡን ውድቅ ያደርጉበታል። ይሁን እንጂ ወቅቱ የበርሊን ግንብ የፈረሰበትና የምስራቁ ዓለም ፍልስፍና እየከሰመ የነበረበት በመሆኑ ሁለቱ

የመኖች በመዋሃድ የየመን ሪፐብሊክ ዳግም ለመወለድ በቃች። በተመሰረተው የጥምር መንግስት ውስጥ የኮሚኒስቶች መካተት ያስቆጣው ኦሳማም የመን በመሄድና በመስጊዶች በመገኘት ቀስቃሽ የሆኑ መንግስትን የሚያወግዙ ንግግሮችን ከማድረግ አልፎ መንግስትን የሚቃወሙ ኃይሎችን በገንዘብ መደገፍ ጀመረ። ሀገራቸው ዳግም ወደ ደም አፋሳሽ የርስ በርስ ጦርነት እንዳትገባ የሰጉት የያኔው የየመን ፕሬዝዳንት አሊ አብደላ ሳላህ የሳዑዲው ንጉስ ፋህድ ዘንድ በመሄድ "ኦሳማን አንድ በሉልን" ሲሉ ይማፀናሉ። በዚህም ኦሳማ ለተወሰኑ ጊዜያት ወደ የመን መሄዱን አቆመ።

ከጥቂት ወራት በኋላም አሜሪካ በየመን የጦር ሰፈር ለመገንባት ስትስማማ ለወትሮ መላው የአረቢያ ልሳነ ምድር ቅዱስ ስፍራ ነው ብሎ ለሚያምነው ኦሳማ የአሜሪካ የጦር መርከቦች በየመን የባህር ዳርቻዎች መገኘት የመርገምን ጨርቅ በተቀደሰ ስፍራ የማኖርን ያህል ሆኖ ተሰማው። በመሆኑም የንጉሱን "እጅህን ከየመን ላይ አንሳ!" ማስጠንቀቂያ ወደጎን በመተው በየመን መስጊዶች በመገኘት ህዝቡ በመንግስት ላይ እንዲነሳ መቀስቀስ ጀመረ። የህዝብ ቁጣ ያሰጋቸው ፕሬዝዳንት አሊ አብደላም ዳግም ወደ ሳዑዲ በመሄድ ለንጉሱ አቤቱታቸውን አቀረቡ። ትዕግስታቸው የተሟጠጠው ንጉስ ፋህድም በሀገር ውስጥ ደህንነቱ ልዑል አልጋወራሽ ናኢፍ አማካኝነት ፓስፖርቱን እንዲቀማ በማድረጋቸው ከሳዑዲ ውጪ ወደየትም እንዳይንቀሳቀስ ተደረገ።

በሌላ በኩል በጁላይ 31, 1990 ዓ.ም ንጉስ ፋህድ በቤተመንግስታቸው የኢራቅንና የኩዌትን ልዑካን ለማደራደር ያደረጉት ጥረት ካለመሳካቱም ባሻገር ከሁለት ቀናት በኋላ ግዙፉ የሳዳም ጦር ኩዌትን በስድስት ሰዓታት ውስጥ ወርሮ ከሳዑዲ የነዳጅ ጉድጓዶች ማዶ በጥቂት ማይሎች ርቀት በድንበር አካባቢ ሰፈረ። ይባስ ብሎም ፍልስጥኤም፣ሱዳን፣አልጄሪያ፣ሊቢያ፣ቱኒዝያ እና ጆርዳን በአደባባይ የሳዳምን ወረራ ደገፉ። በቀናት ውስጥም የሳዳም ጦር የቅኝት ቡድን አባላት የሳዑዲን ድንበር ሲሻገሩ በድንበር ጠባቂዎች ይያዛሉ፤ይህም የሳዳም ፍላጎት ከኩዌት በዘለለ በነዳጅ የበለፀገውን ምስራቃዊውን የሳዑዲ ግዛትም በመውረር አብዛኛውን የአለም የነዳጅ አቅርቦት መቆጣጠር የነበረ ሲሆን ይህም አስተዳደራቸውና ሀገራቸው አደጋ ላይ የወደቀውን ንጉስ በራቸውን ለአሜሪካ ጦር ክፍት እንዲያደርጉ ምክንያት ሆነ። ይሁን እንጂ የአሜሪካ ጦር ሳዑዲ እንዳይሰፍር ኦሳማ ለንጉሱ ደብዳቤ ከመፃፍ ጀምሮ በሃይማኖት አባቶች ቢያስጠይቅም ሰሚ ባለማግኘቱ በእሱና በንጉሳውያን አስተዳደሩ መካከል የማይታረቀው ጠላትነት ተፀነሰ።

በርግጥ ኦሳማም እንደገመተው የኢራቅ ጦር ተሸንፎ ዳግም ላያንሰራራ ወደ ግዛቱ ካፈገፈገ በኋላም የአሜሪካ ጦር መደላድሉን በማስፋት በዚያው በሳዑዲ ቋሚ የጦር ሰፈር ገንብቶ ተቀመጠ። "በተቀደሰው" ስፍራ የአሜሪካ ጦር መስፈሩ ለኦሳማ የእግር እሳት ቢሆንም በአንድ ወቅት የተነጠቀውን ፓስፖርት እንዲመለስለት የንጉሱን አስተዳደር መወትወት ጀመረ። ለዚህም እንደምክንያት ያቀረበው በወቅቱ በአፍጋኒስታን ሙጃህዲኖች መካከል የስልጣን ሽኩቻ በመፈጠሩ የአህመድ ሻህ ማሱድ እና የሄክማትያር ኃይሎችን አስታርቃለሁ የሚል መከራከሪያ ሲሆን የሳዑዲ መንግስትም የኢራንን በምዕራባዊ አፍጋኒስታን ላይ ያላትን ተፅዕኖ በመፍራት ከሱኒ ወገን የሆነውን በሄክማትያር የሚመራውን ኃይል በመደገፍ ወደ ማደራደሩ ስትገባ ኦሳማም ይህንን ሚና የተሻለ ይጫወታል በሚል የሀገር ውስጥ ደህንነቱ ኦሳማን በየትኛውም የአረብ ሀገራት ጉዳይ ላይ እጁን እንደማያስገባ በማስፈረም ፓስፖርቱን ይመልሱለታል። ይሁን እንጂ የአፍጋን ሙጃህዲኖችን ለማስታረቅ ወደ ፓኪስታን ያቀናው ኦሳማ ድርድሩን ከሳዑዲ መንግስት ፍላጎት ውጪ ለማድረግ በመሞከሩ ሽምግልናው ሳይሳካ ይቀራል። በዚህም የሳዑዲ መንግስት ሊገድለኝ ይፈልጋል በማለት በተለይ የሳዑዲ የደህንነቱን ሰው ልዑል አልጋወረሽ ተርኪን በአደባባይ መወረፍ ጀመረ።

በሌላ በኩል ፀረ-ሶቭየት የነበረው ጅሃድ ሲጠናቀቅ ከተለያዩ ሀገራት የመጡት ጂሃዲስቶች ወደየሀገራቸው ሲመለሱ የጠበቃቸው የጀግና አቀባበል አልነበረም ይልቁን የነዚህ ፅንፈኛ ጂሃዲስቶች መመለስ የሀገራቱን መንግስታት ህልውና አደጋ ላይ ይጥላል በሚል ከፊሎቹ ለእስርና እንግልት ሲዳረጉ ከፊሎቹም ወደሀገራቸው እንዳይመለሱ ተደረገ። በመሆኑም ወደ ካሽሚር፣ኮሶቮ፣በስኒያ እና ቼቺኒያ በመሄድ በነዚህ አካባቢዎች ይደረጉ የነበሩ ጦርነቶችን ተቀላቀሉ። ይሁን እንጂ በሰኔ 1989 ዓ.ም. በያኔው ብርጋዲየር ጄነራል በዛሬው ፊልድ ማርሻል ኦማር ሀሰን አልበሽር እና በሀሰን አልቱራቢ የተመራ የተሳካ መፈንቅለ መንግስት በጎረቤት ሱዳን ተካሄደ። ይህንን ተከትሎም የሱዳን መንግስት እነዚያ ሀገር አልባ ለሆኑ ጂሃዲስቶች ማደሪያ ይሆን ዘንድ ጥሪ አደረገላቸው። በመሆኑም በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ጂሃዲስቶች ወደ ሱዳን ተመሙ።

ከዚሁ ጎን ለጎን የሱዳን መንግስት በ1990 ዓ.ም. ኦሳማ ቢንላደን ሱዳንን እንዲጎበኝ ጥሪ አደረገለት። ከዚህ በተጨማሪም የኦሳማ ቤተሰብ ንብረት ለሆነው ሳዑዲ-ቢንላደን ግሩፕ በፖርት ሱዳን የአውሮፕላን ጣቢያ እንዲገነባ ያለጨረታ ከሱዳን መንግስት ተሰጠው። ይህንንም ተከትሎ የግንባታውን ሥራ ለመከታተል ወደ ሱዳን መመላለስ ጀመረ።በ1992 ዓ.ምም አራት ሚስቶቹንና አስራሰባት /17/ ልጆቹን በመያዝ ሱዳንን ቋሚ መኖሪያው ከማድረጉ ባሻገር ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ የኢንቨስትመንት ስራውን ከግንባታ ስራው ጎን ለጎን በግብርናው ዘርፍም በመሳተፍ በሀገሪቱ ሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች፣ በገዳሪፍ እንዲሁም በኢትዮጵያ ድንበር አቅራቢያ በአባይ ወንዝ ምዕራባዊ መፋሰሻ በሆነው በደማዜን አካባቢ ለወጪ ንግድ የሚሆኑ የቅባት እህሎችን ማምረት ጀመረ። ነገር ግን በኢንቨስትመንቱ ስኬታማ ጅማሬ ቢያሳይም የአሜሪካ ጦር በሳዑዲ በቋሚነት መስፈሩ ኦሳማን ዕረፍት የነሳው ሲሆን በአልቃይዳ የፋትዋ ኮሚቴ መሪ በሆነው አቡ ሃጅር አማካኝነት በተሰጠ ፋትዋ /ሃይማኖታዊ ትዕዛዝ/ በአሜሪካ ወታደሮችና ወታደራዊ ተቋማት ላይ አልቃይዳ ጥቃት እንዲፈፅም ትዕዛዝ ተላለፈ። ይህም አልቃይዳን በአለማቀፍ ደረጃ አሸባሪ ድርጅት ተብሎ እንዲመዘገብ ምክንያት ሆነ። ከዚህ ጎን ለጎን በአልጄሪያና የመን ለሚፈፀሙ የሰርጎ ገቦች ጥቃት የነዚህ ሀገራት መንግስታት ኦሳማን ተጠያቂ በማድረግ የሳዑዲ

መንግስት በኦሳማ ላይ እርምጃ እንዲወስድ ጫና ሲያደርጉ ቢቆዩም በኋላ ላይ ግብፅም የዚሁ ሰለባ በመሆኗ የሳዑዲ መንግስት ጫናው ሲበዛበት ማርች 5 ቀን 1994 ዓ.ም. ንጉስ ፋህድ የኦሳማን የሳዑዲ ዜግነት በአዋጅ ነጠቁት።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በኤፕሪል 1994 ዓ.ም. በሱዳን የሚገኙ ፅንፈኛ ድርጅቶች ጠላቶቻችን በሚሏቸው መንግስታት ላይ እርምጃ ለመውሰድ ስብሰባ ያደረጉ ሲሆን ይህንንም የመራው በግብፅ የሚንቀሳቀሰው አል ጂሃድ በመባል የሚጠራው ድርጅት መሪ የሆነው ዶክተር አይማን አልዘዋሪ /ከኦሳማ መገደል በኋላ የአልቃይዳ መሪ ሆኗል/ ሲሆን የሱዳን መንግስትም የጦር መሣሪያ እና ሃሰተኛ ዶክመንቶችን ለማመቻቸት ይስማማል። በመሆኑም ከ አንድ አመት በኋላ ሰኔ 26, 1995 ዓ.ም በአዲስ አበባ ለሚካሄደው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ስብሰባ ለመሳተፍ የግብፁ መሪ ሆስኒ ሙባረክ ከቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ወደ ተዘጋጀለት ማረፊያ እየተጓዘ እያለ ዘጠኝ አባላት ባሉትና ሙስጠፋ ሃምዛ በተባለ ግብፃዊ የአልቃይዳ አባል በተመራ ቡድን የግድያ ሙከራ ተካሄደበት። በወቅቱ በተደረገ የተኩስ ልውውጥ ለሙባረክ የጥበቃ ሽፋን ከሚሰጡ የኢትዮጵያ ወታደሮች መካከል ሁለቱ ሲሰው ከዘጠኙ የአልቃይዳና የአል ጂሃድ አባላት አምስቱ ሲገደሉ፤ አንዱ ያመለጠ ሲሆን ሶስቱ በህይወት ሊያዙ ችለዋል። በመሆኑም የኢትዮጵያ መንግስት በነዚህ ሶስቱ አሸባሪዎች ላይ ባደረገው ምርመራ የሱዳን መንግስት ተሳታፊ መሆኑ ይደረስበታል። ስለሆነም የኢትዮጵያ መንግስት ለተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት በሱዳን መንግስት ላይ ባቀረበው ክስ መሠረት ያለምንም ተቃውሞ በሙሉ ድምፅ በሱዳን መንግስት ላይ ጠንካራ የተባለለት የኢኮኖሚ ማዕቀብ ተደረገ። በወቅቱ ከደቡብ ሱዳን ነፃ አውጪዎች ጋር በሚደረግ ጦርነት ትማቅቅ ለነበረው ሱዳን ይህ አይነቱ ጠንካራ የኢኮኖሚ ማዕቀብ በዚህ ሁኔታ ከቀጠለ ሀገሪቱም እንደሀገር ለመቀጠል የማትችል ከመሆኑ በላይ የአሜሪካ መንግስት በካርቱም የሚገኘውን ኤምባሴውንና ሰራተኞቹን ወደ ኬኒያ ያዘዋወረ ሲሆን በወቅቱ በሱዳን የአሜሪካ አምባሳደር የነበሩት ቲሞቲ ኬርኔ ከያኔው የሱዳኑ ምክትል ፕሬዝዳንት አሊ ኦስማን ጠሃ ጋር ባደረጉት የእራት ግብዣ ላይ ሱዳን ከሽብርተኝነት ጋር በተያያዘ የጠለሸ ገጽታዋን ለመቀየር ጥረት ማድረግ እንዳለባት ከማሳሰብም በላይ አሜሪካ ለድርድር ዝግጁ መሆኗን ይገልፃሉ።

በዚህም መሰረት ከአንድ ወር በኋላ የሱዳን የመከላከያ ሚንስትር የነበሩት ሜጀር ጄነራል አል ፈቲህ ኤርዋ ቨርጂኒያ በሚገኝ አንድ የሆቴል ክፍል ውስጥ የወቅቱ በሱዳን የአሜሪካ አምባሳደር ከነበሩት ቲሞቲ ኬርኔ እና ሌሎች የሲ.አይ.ኤ. ወኪሎች በተገኙበት ምስጢራዊ ድርድር ያደረጉ ሲሆን የአሜሪካ መንግስት በሱዳን በኩል መወሰድ ያለበት ብሎ የዘረዘራቸውን በአምባሳደሩ በኩል ሲያቀርብ የሲ.አይ.ኤ. ወኪሎች ከሱዳን የሚፈልጉት ሁለት ነገሮች ብቻ መሆኑን ይገልፃሉ። የመጀመሪያው ወደ ሱዳን የገቡ ሙጃህዲኖችን ስም ዝርዝር፣የፓስፖርት ቁጥርና የጉዞ ቀናቸውን ዝርዝር ሲሆን ሁለተኛው ጥያቄ "ኦሳማን ከሱዳን ወደ አፍጋኒስታን አባሩት" የሚል ነበር።




በሁለተኛው ጥያቄ ግራ የተጋቡት ጄነራል አል ፈቲህ ኦሳማን የምትፈልጉት ከሆነ አስረን እንስጣችሁ አልያም መጥታችሁ ውሰዱት፤የማትፈልጉት ከሆነም እኛ በዓይነ ቁራኛ እየጠበቅነው ኃላፊነቱን ወስደን በኛ ክትትል ሥር ይቆይ ቢሉም የሲ.አይ.ኤው ወኪል "ኦሳማ ወደ ሶማሊያም ሆነ ሌላ ሀገር እንዳይሄድ፥መሄድ ያለበት ወደ አፍጋኒስታን ነው" በሚል ትዕዛዝ አዘል አቋሙ በመፅናቱ ግራ የተጋቡት ጄነራል የተባሉትን ለማድረግ ተስማሙ።

በመሆኑም ከአራት ዓመት በፊት በብዙ በረከት ተጭኖ የመጣባትን ሱዳን ንብረቱን እንኳ በአግባቡ ለመሰብሰብ በቂ ጊዜ ሳያገኝ ቢያንስ እሱ ባመነው መቶ ስልሳ ሚሊዩን ዶላር የሚገመት ንብረቱን በሱዳን በረሃዎች እንደበተነ ራሽያ ሰራሽ በሆነው ቱፖሎቭ ጄት አውሮፕላን ሜይ 18, 1996 ዓ.ም. ሰዓድ እና ኦማር የሚባሉ ወንድ ልጆቹን አስከትሎ የኑቢያን ምድር ለሁልጊዜው ተሰናበተ።

አሁን ሱዳን ከኋላው ቀርታለች.......................በታላቅ ከፍታ በብረት አሞራ ሆድ እንደተጫነ በአል ሰራዊት ኮረብቶች ማዶ ያለችውን ያቺን የነብዩን ሀገር የአረቢያ ምድር በጠራው ሰማይ ቁልቁል እየተሳለማት፥ ዳግም ላያያት ወደ ተራራማው ሀገር ወደ አፍጋኒስታንም አቀና።

*** የሲ.አይ.ኤው ወኪል ኦሳማን ለምን ወደ አፍጋኒስታን እንዲሄድ እንደፈለገ ምላሽ ይሆናሉ የምንላቸውን ነጥቦች በማካተት ተከታዩን ክፍል በቀጣዩ እትማችን እናቀርባለን።**

**ዋቢ መጻህፍት፦** 1. The Looming Towers, Lawrence Wright 2. No Easy Day, Mark Owen. 3. Man Hunt, Peter Bergen. 4. Solving 9/11, Christopher Bollyn.

## ኢትዮጵያ፡- በጋዜጠኞች ስደትም አንደኛ

Betewedag Adnew/Bayreuth

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ባለፉት አስር አመታት ለስደት የዳረጋቸው ጋዜጠኞች ቁጥር ከአለም አንደኛው ነው ። ሲ.ፒ.ጄ. የተባለው የጋዜጠኞች መብት ተሟጋች ድርጅት ባለፈው ሐሙስ በለቀቀው ሪፖርት በአለፉት አስር አመታት ለስደት የሚዳረጉ ኢትዮጵያውያን ጋዜጠኞች ቁጥር ከአለም አንደኛ ነው ብሏል። በነዚህ አስር አመታት ስልሳ ሁለት ኢትዮጵያውያን ጋዜጠኞች አገራቸውን ጥለው የተሰደዱ ሲሆን፤ ይህም እስርን፣ ጥቃትን እና ማስፈራራትን ሽሸት እንደሆነ ታውቋል። ባለፈው አመት ብቻ አስራ አምስት ጋዜጠኞች ከኢትዮጵያ እንደሸሹ እና ይህም ነፃው ፕሬስ ያለበት ሁኔታ እየከፋ ስለመሄዱ ማስረጃ ነው ሲል ሪፖርቱ ገልጿል። የወያኔ አገዛዝ የግል መገናኛ ብዙሃንን ነፃነት የሚገድብ ህግ ከማውጣት አንስቶ ጋዜጠኞችን እንዳሻው በማሰር፤ በመክሰስ እና በማስፈራራት ከሞላ ጎደል ነፃውን ፕሬስ መዝጋቱ ይታወቃል።

ለዚህም ነው እኛ በውጭ የምንገኝና በነፃው ፕሬስ ድምፃችንን በማሰማት ላይ ያለን ኢትዮጵያውያን ትግላችንን በብዕራችን በማፋፋም ላይ የምንገኘው።ስለሆነም በኢትዮጵያችን ነፃ ፕሬስ እስኪሰፍን ትግላችንን በስደትም ላይ ቢሆን መቀጠሉ አይቀርም።

## በስደትም የሚቀድመን አልተገኘም

Tigist Kurabachew/ Nürnberg

በየዓመቱ ከኢትዮጵያ የሚሰደዱ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በተለያዩ አገራት የፖለቲካ ጥገኝነት መጠየቃቸው እንደቀጠለ ነው።በየዓመቱም በህጋዊና ህገወጥ መልኩ 100ሺ የሚጠጉ ኢትዮጵያውያን በተለያዩ አገራት የፖለቲካ ጥገኝነት መጠየቃቸውን የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን በሚሰጠው መግለጫ እያስታወቀ ይገኛል። ይህ ቁጥር በእርስ በርስ ጦርነት ከምትታመሰው ሶማሊያ ከሸሹት ሰዎች ቁጥር ይበልጣል።

ከነዚህ ኢትዮጵያውያን ውስጥ 84 በመቶ የሚሆኑት ወደ ሶማሊያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ግብፅ እና ኬንያ ሄደዋል። ይህ ቁጥር የተሰበሰበው ስደተኞቹ ከሄዱባቸው አገራት መንግስታት እና ለስደተኛ ድርጅቱ የፖለቲካ ጥገኝነት ለማግኘት ባቀረቧቸው ማመልከቻዎች አማካኝነት ስለሆነ የአጠቃላይ ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን ቁጥር አይወክልም። በያመቱ አገራቸውን ጥለው የሚሰደዱ ቁጥራቸው የማይታወቅ ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ጥገኝነት እናገኛለን ብለው ስለማይገምቱ በተለያዩ ሃገራት በህገወጥነት እንደሚኖሩ ይታወቃል።

በተጨማሪም፥ ቁጥሩ የጉልበት ስራ ፍለጋ ወደ መካከለኛው ምስራቅ እና ሌሎች አገራት በህጋዊ መንገድ የሚሄዱትን የኢኮኖሚ ስደተኞች አያካትትም። የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ያለው የኢኮኖሚ ሁኔታ እየተሻሻለ እና አገሪቱ ወደ ዴሞክራሲ እየሄደች መሆኑን ደጋግሞ ቢናገርም፤ በአስርት ሺሆች የሚቆጠሩ ዜጎች በየአመቱ አገራቸውን እየጣሉ መሰደዳቸው አገዛዙ የሚለው ተቃራኒ እውነት ለመሆኑ ምስክር መሆኑን ልብ ይሏል። ስለዚህ ስደት ለሚያበቃባት ኢትዮጵያ የበኩላችንን ጥረት እናድርግ!

## የወያኔ ፍትሃዊ ምርጫ

Simret Ayalew Mengesha/ Höckstadt

እንደሚታወቀው በሃገራችን በየአምስት ዓመቱ የሚካሄደው ምርጫ ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ ነው እየተባለ በመንግስት መገናኛ ብዙሃን ይለፈፋል።ነገር ግን በተቃራኒው ፍትህ አልባና ኢ-ዴሞክራሲያዊ ነው። ለምን ቢባል ባለው ስርኢዓት አገዛዝ መቼም ቢሆን ህጋዊ ምርጫ አይካሄድምና ነው። ይባስ ብሎ በአሁኑ ወቅት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን ከእረፍት ጊዚያቸው በአስገዳጅ አስቀርቶ በምርጫ ስርዓት ዙሪያ ስልጠና ይሰጣል በሚል ሰበብ ቀጣዩ ምርጫን በአስገዳጅ ድምጻቸውን ለማሰጠት እየጣረ ይገኛል። በቀጣዩ ምርጫ እንደማይመረጥ ወያኔ በመገንዘቡ ህዝቡን በመከፋፈል እንዲመርጠው የማስገደድ ስራውን በገጠርም በከተማም አጠናክሮ ቀጥሎበታል።

በአንፃሩም በጥቅማጥቅም ስም ለመንግስት ሰራተኞች ደሞዝ በመጨመር የትራንስፖርት አውቶቡስ በማዘጋጀትና በመሳሰሉት ምርጫው እስኪያልፍ ብቻ እየተለማመጠ ነው።ታዲያ በራሱ የማይተማመንና ለቃሉ የማይኖር መንግስት አገር ሊያስተዳድር አይችልምና ሊወገድ ይገባዋል!

## ሀገርን ቆርሶ ሸጦ የሌላ አገር ፍለጋ

Fisshatsion Hailegeberile / Kronach

የተከበራችሁ ውድ አንባብያን ሀገራችንን ኢትዮጵያን እንደሚታወቀው የወያኔ መንግስት ማስተዳደር ከጀመረ ከሃያ አመት በላይ ተቆጠረ።ነገር ግን በእነዚህ ዓመታት ውስጥ እየታየ ያለው ለውጥ በጣም የሚያስገርምና እጅግ አስገራሚ ነገሮች እየታዩ ናቸው።እሱም አገር የሚኖረው ዳር ድንበሩ ሲከበር አገርን ሊደፍር የመጣ ጠላት ሲወረር ያንድ አገር ሉዓላዊነት ተከበረ ይባላል።እናም ወራሪው ጠላት አፍሮ ተዋርዶ ይመለሳል።የአገር ዳርድንበር ተከበረ ይባላል።አሁን ወያኔ በተቃራኒው እያከናወነ ያለው ።ስርዓቱ የኢትዮጵያን መሬት ለጎረቤት አገሮች ቆርሶ ቆራርሶ መሸጥ አልያም በስጦታ መልክ መስጠት ተያይዟል።የሚገርመው ወያኔ ባለፍት ዓመታት መልሶ አሳልፎ ለሚሰጠው የባድሜ መሬት እጅግ ብዙ የወገን ደም የፈሰሰበት እና የህይወት መስዋዕት የተከፈለበትን መሬት አሳልፎ ለኤርትራ ሰጠ።ዛሬ ደግሞ ምንም ወዳጅነት ለሌለን አገር ለሱዳን መንግስት የሑመራን መሬት እየቆረሰ እየሸጠ ነው ያለው። ለምን ቢባል ወያኔ እየሰራ ያለው አገርን ቆራርጦ መሸጥ ነውና አላማው።

አንባብያን የቀደሙት አባቶቻችን አገራችንን ያቆዩልን ደማቸውን አፍሰው ህይወታቸውን ሰውተው ነው።እናም እኛ ዛሬ ለተተኪው ትውልድ የምናስረክበው የዛሬይቱን ኢትዮጵ ያ ቆራርሰው ጨረሷት ታዲያ ዛሬ እውን አገራችን ኢትዮጵያ አለች ማለት ይቻላል ወይ?ለመናገር አያስደፍርም ወያ ኔ ግን አሁን ያለውን የአገራችንን ህዝብ በደንብ ሳያስተዳድር ሌላ ተጨማሪ ሱማሌላንድንና ፖርትላንድን ማስተዳደር እችላለሁ የሚል አቋም እያንፀባረቀ ነው። ይሄ የሚያመላክተው የራስን ድንበር ሳያስከብሩ የሌላ ድንበር ጥበቃ

የማይመስል ነውና ወያኔ የመውደቂያ ጊዜው አሁን ነውና ሁላችንም በጋራ እንታገለው።

# የአገር ስሜት ሳይኖረው አገር የሚመራ

**Ribka Lemma Taye/Homberg-Efze**

ወያኔ ኢህአዴግ በ1983ዓ.ም የአፄ ምንሊክን ቤተመንግስት ከተቆጣጠረ ወዲህ ኢትዮጵያዊ የሚለውን መንፈስ ገድሎ የአገራችንን ለም መሬት ለውጪ ሃይላት በመሸጥ ህዝቡን እርስ በርሱ እንዲባላ በማድረግ እድሜ ጠገብ ቤተ እምነቶችን በማጥፋት በአንድ አካባቢ የወጡ የዘር ፖለቲካ አራማጆችና አቀንቃኞች የጦር ሃይሉን በመቆጣጠር ሌላውን አሸባሪና ነፍጠኛ የድሮ ስርዓት ናፋቂ ብሎ በመፈረጅ ኢትዮጵያ ልጅ እያላት እንዳይኖራት በማድረግ የኢትዮጵያዊነት ስሜት ያለውን በሰበብ አስባቡ ቃሊቲ እስር ቤት በማጎር አለዚያም አገር ለቆ እንዲወጣ የፖለቲካ ማህደሩን በማጥበብ አገሪቱ የወላድ መካን አድርጓታል።



በተጨማሪም ታሪኳን የሚያወሱ ዘፋኞችና አዝማሪዎች ሳይቀሩ በቁጥጥር ስር አድርገውታል።ህወሓት ከአመሰራረቱ ጀምሮ ኢትዮጵ የምትባል አገር ለማጥፋት የተነሳ በተለይም አማራውንና የአማራውን እሴቶች ለማውደም የተነሳ መሆኑን ከጅምሩ አሳውቆናል።ስለዚህ እኛ ኢትዮጵያውያን ልዩነታችንን አጥብበን ይህንን ስርዓት በዴሞክራሲያዊ አስተዳደር መለወጥ ይገባናል እላለሁ።

# አምባገነኑ ወያኔ

**Sisay Getachew/Vlotho**

የወያኔ መንግስት ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ሀገርን ማፍረስ ብሔራዊ ጥቅምን አሳልፎ መስጠት ህዝብን በህዝብ ላይ በጎሳና በብሔር ከፋፍሎ በማነሳሳት ባህልንና ቅርስን ማጥፋት አልያም መዝረፍ ከሚታወቅባቸው ዋና ዋና ባህሪዎቹ ናቸው።

ባለፍት ሃያ ሁለት ዓመታት የሃገርንና የህዝብን ሃብት በማግበስበስ የኖረው የህወሓት ቡድን የሚፈጥራቸው የመብት ረገጣዎች ሆነ የሚያጠፋቸው የንፁሃን ዜጎች ህይወት መንስኤው ባለስልጣናቱ አልሞላ ያላቸው ኪሳቸው ነው።በተለያዩ ጊዚያት የስርዓቱ አባላት የሚለፍፉት የኢኮኖሚ እድገት ፕሮፓጋንዳ በአካባቢያቸው ያሉት አባሎቻቸው ኪስ መደለቡን እንጂ ሌላውን ህዝብ እንደማይመለከት ይታወቃል።ታዲያ ይህን እውነታ የሚቃወሙትን ምሑራን ጋዜጠኞች አገር ወዳዶችና ለጋሾችን በማጥላላትና ከአሸባሪ ጋር በመለጠፍ ከአገር ሲገፉም ይስተዋላል።እስሩ ግርፋቱና ሞት ፍርዱም እንደቀጠለ ነው።ከዚህ በተጨማሪ ረዥም ጉዞ በማድረግ ህይወቱን ለማትረፍ ህዝቡ የሚያደርገው ትግል በበረሃና በባህር ስንቱ እንደቀለጠ ቤት ይቁጠረው።ይህም አምባገነኑ የወያኔ መንግስት የሚያደርገው የስውርም ሆነ የሻልፅ ማስፈራራት እስራትና ግድያ ውጤት ነው።ሰለዚህ ድርጊቱ በአስቸኳይ እንዲቆም ጥሪዬን አቀርባለሁ።ድል ለመላው የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች !

# በደሉ ስር ሰዷል!

**Elsa Hagos/ Lahntal**

እንደሚታወቀው በሃገራችን ኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለው ግፍና ጭቆና ከቀን ወደ ቀን ስር እየሰደደ መጥቷል፡፡ ምክንያቱም ገዢው የወያኔ መንግስት ሃገሪቷን መምራት ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷልና፡፡እንዴት ቢባል ገዢው ፓርቲ በስልጣን ዘመኑ ሃገራችንን ብዙ ነገሮች አሳጥቷል፡፡ ለመጥቀስ ያህል እድገቷ ኋላ ቀር ሆኗል፣ በብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መካከል የነበረው መከባበርና መፋቀር ደብዝዞ በምትኩ ጥላቻና መናናቅ ሰፍኗል፣ የሰው ልጅ እንደዜጋ ማግኘት የሚገባውን መብት ተነፍጎ ያለነፃነት በስጋት ኑሮውን ይገፋል፣ የህግ የበላይነት ተረስቶ ማንኛውም የገዢው ፓርቲ አባል የሆነና ትንሽ ስልጣን ያለው ሰው ተነስቶ የፈለገውን ያደርጋል፡፡ ይህ እንዲሆን ያደረገው የወያኔ መንግስት የፈጠረው የአስተዳደር ብልሹነት ነው።የህግ የበላይነት የሚባል ነገር የለም፣ ተጠያቂ ሊያደርገው የሚችል አካል ስለሌለ ያሻውን ይፈፅማል፡፡የሚናገር ወይም የሚቃወም ካለ ይታሰራል።ይሰደዳል ይጋዛል።ይህ እስከመቼ ይቀጥል? ምላሹ ያለው እኛው ጋር ነው።በጋራ እንታገል !

# ጅምላ መፈናቀልና ስደት

**Roza Teshome/ Würzburg**

ዛሬም እንደ ትናንቱ ምንም የማያውቁ ህጻናት ዋይታ!!! የሴቶችና አረጋዊያን ሌላ ዙር መፈናቀል! ሌላ ዙር የጅምላ ስደት መራር መርዶ ከወደ ጋምቤላ እየተሰማ ይገኛል።

የግጭቱ ስረ መሰረት እንዲህ ነው። የህወሓት አገዛዝ የአካባቢውን ማኅበረሰብ በማፈናቀልና ለም መሬታቸውን ቀምቶ በኢንቨስትመንት ስም ባብዛኛው ካንድ አካባቢ ለመጡ የወያኔ አባላት ቀደም ሲል ለሰሩት

ወንጀል ማካካሻ እንዲሆን ታስቦ ካቅማቸው በላይ ቸራቸው። እነሱም ያለምንም ይሉኝታና ያካባቢውን ማኅበረሰብ ያኗኗር ሁኔታ በጭራሽ ከግምት ሳያስገቡ ጌታዋን እንደተማመነች በግ ያካባቢው ማኅበረሰብ ለዘመናት ሲወርድና ሲወራረድ ጠብቆ ያቆየውን ጥብቅ ደን እየመነጠሩ የጣውላና የከሰል ንግድ ላይ ተሰማሩ።

የአካባቢው ማኅበረሰብ ግን የበይ ተመልካች ሆነ፣ ቅሬታውን ለባለስልጣናት አቤት ቢልም ሰሚ አላገኘም። ጭራሽ ይባስ ብለው በቀየው የተገኘውን ሴት ወንድ ሳይመርጡ በፌደራል ፖሊስ በመቀጥቀጥ ብዙዎችን ለሞት ሲዳርጓቸው ሌሎችን ደግሞ ቁስለኛ አድርገዋል። ከሞትና ከመቁሰል የተረፉትም ተፈናቅለው ዱር ገደሉን ቤታቸው አድርገዋል። በሌላም በኩል የግጭቱ ሰለባ የሆኑት ከሌላ ክልል መጥተው ለረዥም ጊዜ ባካባቢው ኑዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያዊን ዜጎችም የግጭቱ ሰለባ ከመሆን አልተረፉም። ኢትዮጵያዊ ከአገሩ ሌላ በእውን ሌላ አገር አለው እንዴ? በተለይ በውጭ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ችግሩን ማስተጋባት ይገባናል ለመፍትሄውም በጋራ መቆም አለብን።ነገ የሚፈናቀለው የእኛንዳንዳችን ቤተሰብ ይሆናልና!

# ኢትዮጵያ ትቅደም !!!

**Girum Kelemu and Netsanet Mamo/Gross gerau**

በልዩነታችን መደሰት የምንችለው በአንድነታችን ላይ መቆም ስንችል ብቻ ነው፡፡አንድ ዜጋ መጀመሪያ ኢትዮጵያ ከሚለው ትልቅ ምሥል መነሳት አለበት፡፡የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች፣ የተለያዩ ሃይማኖቶች እንዲሁም የተለያዩ ባህሎች ባሉባት ኢትዮጵያ ውስጥ፣ የተለያዩ ሐሳቦች ሊንፀባረቁ እንደሚችሉ ይታወቃል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ስንኖር ግን ሁላችንም አንድ ዓይነት ብሔር፣ አንድ ዓይነት ሃይማኖት፣ አንድ ዓይነት ባህልና አንድ ዓይነት ቋንቋ እንዲኖረን አይጠበቅብንም፡፡ በብሔር፣ በሃይማኖት፣ በባህል፣ በቋንቋና አስተሳሰብ ልዩነት ቢኖረንም፣ ሁላችንንም ግን አንድ የሚያደርገን ነገር አለ፡፡ እሱም ኢትዮጵያ የምንላት አገር ናት፡፡ ኢትዮጵያ የሦስት ሺሕ ዓመት ታሪክ ሊኖራት የቻለው አንድነት የሚለው መሠረት ላይ በመቆሚ ነው፡፡ ለዚህ ነው አንድ ዜጋ መጀመሪያ ኢትዮጵያ ከሚለው ትልቅ ምሥል መነሳት ያለበት፡፡ ነገር ግን አንድ ዜጋ ከአገሩ በፊት ብሔሩን ወይም ሃይማኖቱን ወይም ቋንቋውን የሚያስቀድም ከሆነ ሊያስቀድማቸው የፈለጋቸውን ነገሮች ለማግኘት አስቸጋሪ ይሆንበታል፡፡ ምክንያቱም በልዩነታችን መደሰት የምንችለው በአንድነታችን ላይ መቆም ስንችል ብቻ ነው፡፡ ያለበለዚያ ግን በልዩነታችን መደሰት አዳጋች ነው፡፡

## *Pushkin is an Ethiopian !*

**"[There's] no question about Alexander Pushkin being an Ethiopian," Ayalneh Mulatu, who translated Pushkin's poetry into Amharic, the language of Ethiopia, told Anadolu Agency.**

**"Pushkin belongs to Ethiopia because his great grandfather, Abraham Hanibal, was born of Ethiopian parents on Ethiopian soil," he said.**

**Born in 1799 in Moscow, Pushkin is considered Russia's greatest poet and the founder of modern Russian literature.His grandfather, Abram Gannibal, was born in Ethiopia before being brought to Russia as a slave of Russian Czar Peter the Great.**

# ያሁኑ ይባስ

**Jemal Awol kibret / Ehringshausen**

ወያኔ አስራ ሰባት አመት በጫካ በዱላ ለሃይማኖት እኩልነት ለሰው ልጅ መብት ክብር ታግየለታለው የሚለው የስልጣን ጥማት እንጅ እውነት ቀደምት ነገስታት ሲያደርሱ የነበረው ግፍ አንገሽግሾት አይደለም። ለዚህም በትንሹ ማሳያ ወያኔ የሃይማኖትን እኩልነት አስከብራለሁ እያለ በሙስሊሙ ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ከአንድ ሀገር ከሚመራ መንግስት ነኝ ብሎ እራሱን በግድ ስልጣን ላይ ካስቀመጠ አይጠበቅም።ከዚያ በፊት የነበሩት ነገስታት በሙስሊሙ ላይ በርካታ ግፍ ሲፈጽሙበት ቆይተዋል። ይሁን እና ግን የወያኔ ግፍ ከበፊቱ

በከፋና በባሰ ደረጃ ክብር የሆነውን የሰው ልጅ ደም አላግባብ እያፈሰሰ እነሱ አሸባሪ መሆኑን እነሱ እራሳቸው በተግባር አረጋግጠዋል። አሁንም ቢሆን ሙስሊሙ የጠየቀው ሰላማዊ እና ሙስሊሙ ውስጥ ወያኔ ጣልቃ መግባቱን እስካላቆመ ድረስ ከዚህ በፊት እንዳደረግነው ሰላማዊ ትግላችን እስከመጨረሻው ይቀጥላል።





# Fair Election: A tool for real democracy

**Mengistu Asefa/ Vlotho**

The present Ethiopian regime has announced to make an election next year. But still now the regime has limited the right of public meeting or demonstration. According to the regime, the repeated demonstrations in the country are useless and boring. Because of fear, the woyane regime will not allow demos in the future. The regime don`t wants to give a direct response for the questions of the people, that's why: - there are repeated demos here and there. Without opposition parties, what kind of election will be conducted? It is a day light nightmare.

I think the regime did not recognize the rules of law and election process. If the Ethiopian government did not respond I think any one has a natural right to peaceful rally as long as the government is giving real answer not the one as TPLF giving. The difference of the Ethiopian government and others is the Ethiopian government did not hear its peoples where as the other respect the right of its people. We know the result of the next election, so why donor governments spend much money for one party election. This will be unacceptable and if they tried to do it, it showed us that they have no respect for their tax payers too. We need a fair election in Ethiopia!God bless Ethiopia.

# Private press crackdown!

**Abdi Zeki Kerim/ Fulda**

The recent charges of five magazines a news paper by the ministry of justice clearly indicated that freedom of expression is in crackdown in Ethiopia. As a result of the charge, critical voices are being strongly diminishing. In a press release issued August 4/2014, the ministry of justice accused the publications(Afro Times,a weekly newspaper and magazines Addis Guday,Enku,Fact,Jano and Lomi) `` of publishing false information ,inciting violence and undermining public confidence in government``.

Following the charges on these private Medias by the government, some 12 Journalists fled the country in a week period only. Addis Guday`s Managing director, Endalekachew Tesfaye,Deputy Editor in Chief Ibrahim Shafi,Senior editor Endale Teshi and Columnist Habtamu Seyoum, and Lomi`s owner Gizaw Taye,Daniel Dirsha, and Senay Abate and two columinists of the same publication have fled the country. Besides, Afro Times and Jano`s publishers Thomas Ayalew and Asnake Lebawi respectively, and Dawit Solomon of Fenote Netsanet have also fled the country. Accordingly, the number of Journalists who fled the country has reached 12 in a week.

# Innocents are still Vulnerables

**Hilina Dawit/ Nürnberg**

Wrapped in dishonesty, arrogance and paranoia, Ethiopia's ruling regime is following a nationwide policy of violent suppression and constitutional vandalism.

The regime in Ethiopia has no compromisation to oppress and demolarized all catagories of people. Even you are a journalist a politician a farmer young old child, no matter what you will go to prison, if your attitude is against the regime´s propaganda.

Many of them had been unfairly tried in presence or absentia every year. according to reports ,most of them "sentenced to death for an alleged coup attempt,the so called terrorism act and so on. alongside other prisoners of conscience, and sentenced to life imprisonment."

Incarcerated them remains, hidden, abused and tortured by Ethiopian military thugs. Their "detention in Ethiopia means that their life and physical integrity are in great danger… their incommunicado detention in an unknown location increases this risk". So, we should have to increase our effort to have a democratic system in our beloved country !

# A closed window of opportunity for the coming election in Ethiopia

**Desalegne Abebew and Yalemwork Meswaet/Schöneck**

The ruling junta (TPLF) in Ethiopia is on the way for easy win in the coming fake election. TPLF is doing so much to weaken its opposition parties and to set up the outcome in advance that they will not face any problem of competition. The National Electoral Board of Ethiopia is unable to create a conducive environment to carry out a standard election since all of them are members of the ruling party. Their board has already become an obstacle for unification of two big parties called Unity for Democracy (UDJ) and All Ethiopian Unity Party (AEUP) even though they have signed a pre-coalition agreement that would pave a way for the total union of the parties. From the beginning, members and activists of the parties are beaten, jailed and murdered.

TPLF is using a combination of harassment and arrests and withholding food aid and job to frustrate or spoil the opposition. They want to totally block any opposition presence in the next election. The government dismisses opposition charges of harassment as false. It says economic growth in Ethiopia of more than 11% annually is the main reason it will win re-election. But, Ethiopia is the first by starvation in Africa.

Ethiopia receives billions of dollars for development aid in Ethiopia from U.S., U.K., the World Bank and other donors. But, TPLF uses this money for training its members and for its security purpose instead of social development and good governance.
On the other hand, the TPLF government has effectively disbanded the leadership of the opposition and undercut its ability to undertake any effective challenge during election. The U.S. and E.U. have not criticized the growing authoritarianism of TPLF.
They have seen largely silent on human rights issues as long as TPLF is a key ally in the fight against Islamic militants in neighboring Somalia. This implies unless we Ethiopians stand united and fight for democracy, freedom, justice and fair election in our country, there is no any foreign force who will deliver our freedom in to our hands. God Bless Ethiopian nation and nationalities!!!

# The Ethiopian authorities using a repressive anti-terror law as a pretext to crush dissent people

**Belay Fikre /Ehringshausen**

The Ethiopian authorities must halt their continuing onslaught on dissent Amnesty International said last month. After the arrest of four more opposition party members last month who are still believed to be at risk of torture or other ill treatment. All four were arrested on July in Addis Ababa and the Northern city of Mekele on "terror" accusations, a charge commonly used as a pretext to put dissenters behind bars in Ethiopia.

These latest detentions add to Ethiopia ever increase number of journalist opposition "terrorism offences" said Amnesty International. In the run-up to next year's general election, the fear is that this number will continue to grow as the government continues its onslaught on dissent people. Everyone who has been arrested because of their peaceful expression of dissenting opinions their blessing activities, membership, of a legally registered political opposition party or participation in peaceful protest must immediately and unconditionally released. **God Bless Ethiopia!**

# Solidarity for freedom & justice in Ethiopia

**Nahom Woldeyohannes/ Frankfurt**

What does it takes to agree on the rights of the people of Ethiopia regardless of their ethnicity political view and religious affiliation to decide their own fate who should govern them?the fact remained;no one represents anyone until the people say so in their free will. TPLF is the ruling party that permits no competing institutions or success of independent power in Ethiopian political landscape at all.

Once again in the last few months, the brutal TPLF regime in Ethiopia has detained and falsely charged journalists' bloogers civil right activists' political leaders and several other individuals. Regardless of how one looks at it what happened to the vulnerables of the regime. ``Torture`` in vilolation of Ethiopia`s constitution and international human rights conventions. Therefore it is easy for woyane to label one group or another as terrorist and get away with murder.Ethiopia`s gov`t,a staunch western ally in a poor and violent region ,has a track record of jailing Journalists and political activists`,often using a so called anti terrorism law. We Ethiopians in abroad have been closely following political developments in the country, and political and economical conditions in Ethiopia have never been as scandalous and hostile as they are now.

Now adays, arresting and torturing citizens in Ethiopia is a normal business of this ruthless regime. The purpose of the politically motivated arrests and false accusations of the last few months is clear and simple; it is to fill fear in the mind of Ethiopians. The time has come for all Ethiopians without exception to burry the ethnic apartheid regime and move on to better alternative.one lesson Ethiopians should learn by now is the struggle torid of tyranny is a collective struggle for democracy. There is no ethnic religious and region devides when it comes to democracy and freedom. The time has come to put down tyranny in its knees and build democracy once and forever.our struggle should be for national unity under one national flag shall be firm without misleading anyone. The burden is on us to keep this movment a struggle for justice,freedom and democracy.

# Attack on critical Voices

**Yoseph Teklu/ Fulda**

Now, Ethiopia as a whole and addis ababa in particular is depressing as most of the magazines and news papers which are charged have gone out of print. Some stopped publishing sooner as the charges aired on Ethiopian Television, the major mouthpiece of the government. Addis Guday magazines stopped publishing on august 9, and three others did the same in the following days. The publications were prevalent alternatives to the state run press and TV and radios, which, almost always, narrate only positive narratives.

The incumbent Ethiopian government has a trend to use various means to silence critical voices whenever it likes with no considerations of legislations. It was remembered that the regime did the same during the 2005 national election. The recent charges could also be a way to silence critics ahead of elections expected in May 2015.

Off late, in February, the government run Ethiopian Press Agency in collaboration with a certain institution , conducted a so called tendency study (Yeazmamiya Tinat) aimed at analayzing the content of some publications. The study concluded that some publications, the recently charged ones, were responsible for inciting violence and upholding opposition view points. This time, many journalists were sure that the government was planning to charge the publications . and they were right,the regime did it.